# የሚስዮን መለኮታዊ ጥሪ

ካህን ሮናልድ ኤ ራዝባንድ
የሰባዎቹ ቡድን አመራር አባል

ውድ የክህነት ስልጣን ወንድሞቼ ፣ በዚህ ምሽት ስለሚስዮን አገልግሎት ለመናገር እፈልጋለሁ። ንግግሬንም በአለም ውስጥ ለተሰበሰቡት የአሮናዊ የክህነት ስልጣን ላላቸው ወጣት ወንዶች እና ለአባቶቻቸው፣ ለአያቶቻቸው፣ እና ለእክህነት ስልጣን መሪዎቻቸው ለማተኮር እፈልጋለሁ።

የሚስዮን ስራ "በእያንዳንዱ ከተማ እና ቦታ ሂዱ፣ የትም ብትሄዱ እዛም እመጣለኡ" ብሎ ጌታ የመደባቸው ሰባዎች እንደሚሰማቸው እኔንም ይሰማኛል። የሚስዮን ስራ የቤተክርስትያኗ የህይወት ደሚ እና መልእክቱን ለሚቀበሉትም ህይወት የሚያድን በረከት ነው።

መምህርት በሰዎች መካከል እያገለገለ እያለ፣ የጋለሊ አሳ አጥማጆችን ማጥመጃቸውን ትተው እንዲከተሉት ጠራ። "የሰው አጥማጆች አደርጋቸውለሁ፡ ብሎም አወጀ። ሌሎች ከእነርሱ የወንጌሉን እውነት ሰምተው እንዲመቱም ዘንድ ትሁተኛ ሰዎችን ነበር የጠራው።

በሰኔ 1837 ዓ/ም፣ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ሂበር ሲ ኪምባልን ወደ እንግሊዝ እንዲሄዱ ጠራቸው። የካህን ኪምባል ጥሪ የመጣው ሁለቱ በከርትላንድ ቤተመቅደስ ቁጭ ብለው እያሉ ነበር እና ጆሴፍም በመለኮታዊ ስልጣን እንዲህ አለ፤ "ወንድም ሂበር፣ የጌታ መንፈስ እንዲህ ብሎኛል፤ 'አገልጋዮ ሒበር ወደ እንግሊዝ ይሂድ እና ወንገሌን ያውጅ እና ለእዚያም አገር የደህንነትን በር ይክፈት።'"

ያ የመንፈስ ማስሾክሾ ለጌታ አገልጋዮች ሚስዮኖችን ወደሚያገለግሉበት ቦታ እንዲሄዱ የሚጠሩበት ምሳሌ ነው።

ዛሬ ሚስዮኖች ያን አይነት መልእክት በመያዝ፣ ከእግዚአብሔር ነቢይ በሚመጣው በዚያም አይነት መለኮታዊ ጥሪ በጌታ እንደተመደበው ሁለት በሁለት  ይሄዳሉ። ፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን እንዲያገለግሉ ለተጠሩት እንዲህ ብለዋል፤ "በህይወት የሚገኝ ሚስዮንነ የመሆን እድል የእናንተ ነው። የዘለላለም በረከቶችም ይጠብቋችኋል። መብታችሁ ተመልካቶች እንድትሆኑ ሳይሆን በክህነት ስልጣን አገልግሎት ተሳታፊ እንድትሆኑ ነው።"

ውድ የአሮናዊ ክህነት ስልጣን ልጆች፣ እድሉ የእናንተ ነው። ሀላፊነታችሁን ለማሟላት ተዘጋጅታችኋል? በዚህ ምሽት ጀምሮ የሚችለው እያንዳንዱ ወጣት ሰው በእግዚአብሔር ነቢይ ለሚመጣው የሚስዮን አገልግሎት ብቁ ለመሆን እንዲዘጋጅ ጌታ ይፈልጋቸዋል።

ሁለቱ ልጆቻችን የሚስዮን ጥሩ ሲያገኙ እንዴት እንደተደሰትን አስታውሳለሁ። ከእግዚአብሔር ነቢይ የመጣውን ልዩ ደብዳቤ ሲከፍቱ ደስታ እና ጉጉት ልቦቻችንን ሞሉት። ልጃችን ጀኔሳ ወደ ሚሽጋን ዲትሮይት ሚስዮን ተጠራች እና ክርስትያንም ወደ ራሽያ ሞስኮ ሚስዮን ተጠራ። እንዴት ትሁተኛ የሚያስደርግ እና አስደሳችአጋጣሚ ነበር።

እህት ራዝባንድ እና እኔ ከብዙ አመታት በፊት በNY NY ሚስዮን አመራር ለመሆን እድል ነበረን እና ሚስዮኖቹ ወደ እዚያ ሲደርሱ እንገረም ነበር።

ሚስዮኑ በደረሱበት በመጀመሪያው ቀን ለእያንዳንዶቹ ሚስዮን ታላቅ ምስጋና ነበረኝ። የተጠሩበት ሚስዮን ለእነርሱ እና እንደ ሚስዮን ፕሬዘደንታቸው ለእኔ በመለኮታዊነት የተነደፈ እንደሆነ ይሰማኝ ነበር።

በሚስዮን የተመደብንበትን ከፈጸምን በኋላ፣ እንደ ቤተክርስትያኗ ሰባዎች ቡድን አባል በፕሬዘደንት ሒንክሊ ተጠርቼ ነበር። እንደ አጠቃላይ ባለስልጣንነት ከተሰላጠንኩበት መጀመሪያ አንዱ ከአስራሑለቱ ሐዋሪያት ቡድን አንዱ ጋር በቤተክርስትያኗ 300 ሚስዮኖች ውስጥ እንዲያገለግሉ ሚስዮኖችን የመመደብ እድል ነበር።

ከፕሬዘደንት አይሪንግ የአስራሑለቱ ሐዋሪያት ቡድን አባል ሆነው እያሉ ከእርሳቸው ጋር የነበረኝን ልዩ አጋጣሚ እንድነግራችሁ ፈቃድ አግኝቼአለሁ። እያንዳንዱ ሐዋሪያት የመንግስት ቁልፍ ይይዛሉ እናበቤተክርስትያኗ ፕሬዘደንት አመራርም እነዚህን ይጠቀሙባቸዋል። ካህን አይሪንግ ሚስዮኖችን እየመደቡ እያሉ እኔ መጥቼ እንድመለከት ተጋብዤ ነበር።

አንድ ጠዋት ለዚህ ጉዳይ ብዙ ትልቅ ኮምፒተሮች በነበሩበት ክፍል ውስጥ ከካህን አይሪንግ ጋር ተገናኘሁ። በእዚያም ቀን እንዲረዱ የተመደቡ በሚስዮን ድፓርትመንት የሚሰሩም ነበሩ።

መጀመሪያ ለጸሎት አብረን ተንበረከክን። ሚስዮን የት ማገልገል እንደሚገባቸው "በፍጹም" ለማወቅ ፕሬዘደንት አይሪንግ እንዴት እንደጸለዩ አስታውሳለሁ። "በፍጹም የሚለው ቃል ካህን አይሪንግ ምን አይነት እምነት በእዚያ ቀን እንደነበራቸው ያሳያል።

ስራው ሲጀመርም፣ የሚመደበው ሚስዮን ፎቶ በአንድ ኮምፒውተር ላይ ይመጣል። እያንዳንዱ ፎቶ ሲመጣ ለእኔ ሚስዮኑ በክፍሉ ውስጥ ከእኛ ጋር የተገኘ ይመስለኝ ነበር። ካህን አይሪንግ እያንዳንዶቹን ሚስዮኖች፤ "መልካም ቀን ካህን ሪር ወይም እህት ያንግ"

እንዴት ናችሁ ዛሬ" በማለት ሰላም ይሏቸው ነበር።

በአዕምሮአቸው ሚስዮኖቹ አገልግሎታቸውን የት እንደሚጨርሱ ለመመልከት እንደሚያስቡ ነገሩኝ። ይህም የት መመደብ እንዳለባቸው እንዲያውቁ ይረዳቸዋል። ከዛም ካህን አይሪንግ የኤጲስ ቆጶስንና የስቴክ ፕሬዘደንትን አስተያየት እና ሌሎች ጉዳዮችን ያጠናሉ።

ከዛም በአለም ውስጥ ያሉትን የሚስዮን ቦታዎችን ወደሚያሳይ ወደሌላው ኮምፒውተር ይመለከትሉ። በመጨረሻም፣ በመንፈስ እንደሚመሩበት ሚስዮንን ወደሚያገለግልበት ቦታ ይመድባሉ።

ከሌሎች አስራ ሑለትም ይህ ዘዴ ሐዋሪያቱ ብዙ ሚስዮኖችን በአለም ሁሉ ሲመድቦ የሚደጋግሙት እንደሆነም ተምሬአለሁ።

በሀገሬ በሚስዮን በማገልገሌ፣ በዚህ አጋጣሚ ዝልቅ ስሜታ ነበረኝ። ደግሞም፣ እንደሚስዮን ፕሬዘደንት በማገለግልበት ጊዜ ወደNY የመቱት ሚስዮኖች የተላኩት በራዕይ እንደሆነ ተጨማሪ ምስክር በማግኘቴም ምስጋና ይሰማኛል።

ትንሽ ሚስዮኖች ከተመደቡ በኋላ፣ ካህን አይሪንግ ስለአንድ ሚስዮን ሲያስቡ ወደ እኔ ዞር ብለው "ወንድም ራዝባንድ ይህ ሚስዮን የት ይሂድ?" ብለው ጠየቁኝ። ደነገጥኩኝ እና ለካህን አይሪንግ አላውቅም እና ማወቅ እንደምችልም አላወቅኩም ነበር አልኳቸው። በቀጥታ ተመለከቱኝ እና እንዲህ አሉኝ፤ "ወንድም ራዝባንድ በትኩረት ተመልከት እና ልታውቅም ትችላለህ።" በዚህም በእርሳቸው አጠገብ ለመቀመጥ ወንበሬን ወደእርሳቸው ወስቼ በትኩረት ማየት ጀመርኩኝ።

ስንቀጥልም፣ ካህን አይሪንግ ወደ እኔ ዞር ብለው፣ "ወንድም ራዝባንድ ይህ ሚስዮን የት መሄድ እንዳለበት ይሰማሀል?" ብለው ይጠይቁኛል። የሚስዮን ማገልገያ ቦታ እጠራለሁ እና እርሳቸውም እየተመለከቱኝ፣ "አይደለም" ይሉኛል።እና በሚነሳሱበት ሚስዮኖችን በመመደብ ይቀጥላሉ።

በዚያ ቀን የምንመድብበትን ለመጨረስ ስንደርስ፣ የአንድ ሚስዮን ፎቶ በኮምፒውተሩ ላይ መጣ። ይህ ሚስዮን በጃፓን መመደብ እንዳለበት ታላቅ ስሜታ ተሰማኝ። ካህነ አይሪንግ ስለዚህ እንደሚጠይቁኝ አላወቅኩም ነበር፣ ግን ጠየቁኝ። በትህትና "ወደ ጃፓን ይሂድ" አልኩኝ። እርሳቸውም "አዎን ይህን ሀገር እንመልከት" አሉ። በጃፓን የሚገኙት ሚስዮኖች በኮምፒውተር ላይ ሲመጡም በሳፖሮ ጃፓን መሄድ እንደሚገባው ወዲያው አወቅኩኝ።

ካህን አይሪንግ ወደየትኛው ሚስዮን መሄድ እንዳለበት አልጠየቁኝም፣ ነገር ግን በሳፖሮ ጃፓን መደቡት።

ሚስዮኑ የት መሄድ እንዳለበት በማወቅ ለተሰማኝ መነሳሳት ጌታን በልቤ እንደተነካሁ ምስጋናዬን አቀረብኩለት።

ከጨረስን በኋላ ካህን አይሪንግ ወደአለም ወጥተው ዳግሞ የተመለሰውን ወንጌል ለመስበክ ለሚሄዱት ሚስዮናት ጌታ ምን ያህል ፍቅር እንዳለው ምስክራቸውን ሰጡኝ። እነዚህ ሚስዮኖች የት መሄድ እንደሚገባቸው የሚያውቁት በጌታ ፍቅር በኩል እንደሆነም ነገሩኝ። በቤተክርስትያኗ የሚመደቡት ወይም ደግመው በሌላ ቦታ የሚመደቡትእያንዳንድ ሚስዮኖች የሚጠሩት በእነዚህ አገልጋዮቹ አንዱ በሁሉን ቻይ አምላክ ራዕይ  እንደሆነ ተጨማሪ ምስክርንም አገኘሁ።

በዳግሞ መመለስ ጊዜ ብዙ ሀላፊነት ለነበራቸው ለውትመር ወንድሞች ጌታ በተናገራቸው ቃላት ይህን እጨርሳለሁ።ለወርቁ ሰሌዳ ምስክሮች ነበሩ እና የፈረሙት ምስክራቸውም በታተሙት መፅሐፈ ሞርሞኖች ውስጥ ሁሉ ይገኛሉ። የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲሰብኩ በ1829 ዓ/ም በእግዚአብሔር ነቢይ ከተጠሩት የመጀመሪያ ሚስዮኖች መካከል አንዱም ነበሩ።

በትምህርት እና ቃል ኪዳን 14 መጀመሪያ ላይ እንዲህ ይላል፤ "ሶስቱ የዊትመር ወንድ ልጆች እያንዳንዳቸው የስራውን እውነትነት ምስክርነት ስላገኙ፣ የእያንዳንዳቸውን ሃላፊንተ በተመለከተ

በጣም አሳስቧቸው ነበር።”

ለጆን እና ለፒተር ውትመር ጌታ እንዲህ አል፤ “ስለሆነ ብዙ ጊዜ ላንተ ትልቅ ዋጋ ስላለው ነገር ምን እንደሆነ ከኔ ለማወቅ ፈልገሃል።”

ብዙዎቻችሁ ወጣቶች ይህን ጥያቄ እራሳችሁን እንደጠየቃችሁ አስባለሁ። ይህም የጌታ መልስ ነው፤

“እናም አሁን፣ እነሆ፣ እንዲህ እልሃለው፣ ላአንተ ታላቅ ዋጋ ያለው ነገር፣ ነብሶችን ወደ እኔ ታመጣ ዘንድ ከእነሱ ጋር በአባቴ መንግስት አብረህ ታርፍ ዘንድ ለዚህ ህዝብ ንስሃን ማወጅ ይሆናል።”

በዚህ በህይወታችሁ ጊዜ ከጌታ የሚስዮን ጥሩ ከምትሰሩት ሁሉ በላይ አስፈላጊ የሆነ ነው። አሁን ተዘጋጁ፣ በጻድቅነት ኑሩ፣ ከቤተሰቦቻችሁ እና ከቤተክርስትያን መሪዎቻችሁ ተማሩ። የእግዚአብሔርን መንግስት ለመገንባት ከእኛ ጋር ኑ---“በዚህም ታላቅ ስራ” መለኮታዊ ምድባችሁን ተቀበሉ።

ይህም ትሁታዊ ጸሎቴ የሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፣ አሜን።